Public Health
Seattle & King County

## የማህበረሰብን ድምፆች ማእከል ማድረግ- የኪንግ ካውንቲ ወረርሽኝ ወይም ፓንደሚክ ምላሾችን የተመለከተ አስተያየት

የሬንየር ቫሊ አዋላጆች በሆኑት ቴራ ላውል እና ጆዲሊን ኦወን ፣ ከሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና ክፍል ሰራተኛ ጌብርኤል ስፐትዘር  ጋር የተዘጋጀ

ባለፈው ዓመት COVID-19 ክልላችንን ማትቃት ሲጀምር ለደንበኞቻችን ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ወዲያውኑ አየን። የሬንየር ቫሊ አዋላጆች (RVM) በሲያትል አካባቢ የወላጆች እና የሕፃናት ጤና ውጤቶችን ለማሻሻል ከነፍሰ ጡር እናቶች ጋራ እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይሠራል። ይህ በሽታ በየቀኑ የምንጋፈጠውን የዘር ኢ-ፍትሃዊነትን እንደሚያባብሰው እናውቅ ነበር - በተጨማሪም እኛ በምናገለግላቸው ሕዝቦች ውስጥ ያልተመጣጠነ ዝቅ ያለ አገልግሎት ለእርጉዝ ሴቶች እንዲሰጥ እና ይበልጥ ሕዳናት ያለቀናቸው እንዲወልዱ ሊያደርግ ይችላል።

አንደኛው አሳሳቢ ምሳሌ - በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ጥቁሮች እና የነባር ተወላጅ ነፍሰ ጡር ሴቶች የሚደርስባችው የጨቅላ ህጻናት ሞት መጠን ከካውንቲው በአጠቃላይ ከሚከሰተው ሁለት እና ሦስት እጥፍ ነው።



*ደራሲዎቹ ፣ ቴራ ላውል እና ጆዲሊን ኦወን ፣ ከሬኒየር ቫሊ አዋላጆች።*

የእኛ መነሻ ታሪክ - የእኛ ማንነትና እና ምንነታችን - በሬንየር ቫሊ ውስጥ በተለምዶ ከሚገለሉ ሰዎች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። እኛ የቆዳ ቀለም ያላቸው ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ትግሎች እና ጥቃቶች ፣ በተለይም በስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ላይ የሚያጋጥማቸውን ትግሎች እና ጥቃቶች በሕይወት ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ የዘረኛነት እና የጾታ ጥላቻን በተማለከተ ጥልቅ የግል ግንዛቤ አለን። በወሊድ እና በስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ውስን አነስተኛ አማራጮች ማግኘትን በተመለከተ የግል ተሞክሮም አለን። ቤተሰቦቻችን እና ጓደኞቻችን የጤና አገልግሎት እድል ለማግኘት የሚጋፈጧቸውን መሰናክሎችን የማየት ልምድ አለን። ሰዎች በሚኖሩበት ሁኔታ ምክንያት ብድር አለመስጠት ፣ የማዳላት የብድር አሰራሮችን ፣ አዳልቶ የመቅጠር ልምዶችን እና ሌሎች ተቋማዊ ዘረኝነትን የሚያሳዩ ተግባሮች ሲፈጸሙ የማይት የግል ልምድ አለን።

የነዚህ ኢ-ፍትሃዊነት መጠን እንደ 2020 የበለጠ ጎልተው አያውቁም። በመጀመሪያ COVID  ሲከሰት ፣ ለመውለድ ዝግጅት ላይ ያሉ ቤተሰቦች አሁንም የእንክብካቤ እና የመውለድ አገልግሎት አማራጮች በ

COVID ወረርሽኝ ወቅት እንዲኖራቸው ፣ ጤት የሚያጠቡ የቤተሰብ ቡድኖችን ወደ ምናባዊ ቡድን በመለወጥ ፣ አስፈላጊ ነገሮችን በቀጥታ ለቤተሰቦች በማድረስ እና ግርግር ላይ ያለውን የጤና እንክብካቤ እንዴት ስርዓት ማስያዝ እንደምንችል የማሰስን እርምጃ ወስደናል። እኛ ማለት እንደምንወደው ፣ በሳጥን ውስጥ ብቻ የምናስብ አይደለንም - ለቤተሰቦች እና ለማህበረሰባችን ሳጥኑን በመፍታት እውነተኛ መፍትሄዎችን ለማግኘት የምንጥር ነን።

ወረርሽኝ በሚከሰትበት ጊዜ ነፍሰ-ጡር ሴቶች እንዴት እንደሚደገፉ ለማወቅ ስንቸገር ፣ የሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና ክፍል የ COVID-19 ወረርሽኝን መቆጣጠር ከ ጥቁሮች ፤ ነባር ተወላጆች እና የቆዳ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች (BIPOC) የሚጎዱት የጤና ልዩነቶች ከመጋፈጥ በፍጹም ተነጥሎ የሚታይ እንዳልሆነ እየተገነዘበ ነበር። በግንቦት ወር የፌንየር ቫሊ አዋላጆች ጥረቱን እንዲቀላቀሉ በተጠየቁ ጊዜ ፤ የማህበረሰብ ጤና ቡድኑ ከማህበረሰቡ ጋር - በመላው ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከተመሰረቱ ቡድኖች ጋር ከድርጅቶች እና ግብረ ኃይሎች ጋር ወደ ተግባር ገበቶ ለወረርሽኙ ምላሽ አብረው እንዲሰጡ እያደረጋ ነበር።

## ወረርሽኝ እና ዘረኝነት - ፀደይ እና በጋ ፣ 2020

አብዛኛው ሥራ በመጋቢት 2020 በየሳምንቱ መገናኘት ወደጀመረው ወደ የወረርሽኙ የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን ተጣምሮ ነበር ፤ ቡድኑ የተዋቀረው በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከሚገኙ የተለያየ መሰረት ካላቸው ማህበራትና አጋር ተቋማት ጋር የተያያዘ ነው።

ስራው የተጀመረው የማህበረሰብ ጤና ክልል የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ ለማህረሰቡ ቃል ለማድረስ፥ ጭምብሎችን እንዲለብሱ ፣ የማህረሰብ ስብሰባን እንዲያስወግዱ እና እጆችዎን እንዲታጠቡ ነበር። ነገር ግን በበሽታው ወረርሽኝ ወቅት ይህ ቡድኑ ከፍተኛ ለውጥ አካሂዷል።

በሰኔ ወር ፣ በመላ አገሪቱ ያሉ ሰዎች መዋቅራዊ ዘረኝነትን እና የፖሊስን ጭካኔ ተፀይፈው በህብረት በተነሱበት ጊዜ ፣ የወረርሽኙ የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን ዘረኝነት በማህበረሰቡ ጤና ላይ ያስከተለውን ቀውስ ወደ ተልእኮው ለማካተት ወሰነ - የወረርሽኝ የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን ( PCAG) ወደ የወረርሽኝ እና ዘረኝነት የማህበረሰብ አማካሪ ቡድን ( PARCAG) ተቀየረ።

ከጊዜ በኋላ የ PARCAG ትኩረት ወደ በማህበረሰብ-የሚንቀሳቀስ አቀራረብ ተሸጋገረ። ሃሳቡን በማስፋትም ከዚህ በፊት ተትተው የነበሩ ድምፆችን አካተተ።

እነዚያ ስብሰባዎች ብርቱ ነበሩ ፣ እናም የበለጠም ብርቱ እየሆኑ ሄዱ። በተለይ የአካል ጉዳት ባለባቸው ሰዎች ህብረት በጣም ልዩ ስሜት ተሰምቶናል። የእነሱ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ኪምብርሊ መክን ፣ ስለ ማህበረሰቧ ጥብቅና ስትቆም እና በማህበረሰብ ጤና ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን መርምራ በማድረግ ስትሟገት ማየት አስገራሚ የጥብቅና ዋና ትምህርት ነበር።

ሥራችን ከእርሷ ማህበር ጋር ፣ እና በኪንግ ካውንቲ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ፣ ከማህበረሰብ ጤና ቦርድ ጥምረት ፣ ከካሳ ላቲና ፣ ከአሜሪካ ህንድ ጤና ኮሚሽን እና ከሌሎች በርካታ የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የሚገናኝባቸውን መንገዶች ሁሉ አይተናል።

በ PARCAG ስብሰባዎች ፣ እኛ በ ሬንየር ቫሊ አዋላጆች ማህብር ( RVM) ስብሰባዎች ላይ የምንጨነቅባቸውን  መከራዎች እና መብትን የማጣት ጉዳዮች ገልፀዋል ፣ ነገር ግን ይኋው እነሱ ፣ በትክክል ጮክ ብለው ይናገሩታል! በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ላሉ ማህበረሰቦች በጣም አስፈላጊ የሆኑ እጅግ የብዙ ጉዳዮች የላቀ ግንኙነት እና ትኩረት ነበር።

**ማን ይመራዋል? -  በልግ፤ 2020**

በበልግ ወራት ፣ አ PARCAG ሌላ ለውጥ አደረገ - ኪንግ ካውንቲ የዚህን ድርጅት መሰረት አመራር ለአባላቱ አስረክቧል። አምስት በማህበረሰብ ለይ ከተመሰረቱ ድርጅቶች እና አንድ ከህዝብ ጤና ክፍል የተውጣጡ ተወካዮች ያሉበት አዲስ መሪ ኮሚቴ ሥራውን መምራት ጀምሯል።

መጀመሪያ ላይ ፣ በማህበረሰብ ለይ የተመሰረቱ ድርጅቶች ኪንግ ካውንቲ ስብሰባዎቹን በሚመራበት ጊዜ አብረው ይከተሉ ነበር። እንዲሳተፉ መጠየቁ በራሱ መሻሻል ነበር። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን እኛ የሃይል አቅማችንን እንድናሳይ ተጠየቀናል። ስብሰባዎችን እንመራ ጀመር። የአጀንዳውን አቅጣጫ እንመራ ነበር። ስንችል ፖሊሲዎችን መምራት ጀመርን። በካውንቲው ድጋፍ ፣ የወረርሽኝ እና ዘረኝነት የማህበረሰብ አማካሪ ቡድንን ወደ ጡንቻማ ፣ ጠንካራ ፣ በማህበረሰብ የሚመራ ጥርሳማ ድርጅት አደረግነው።

በአማካሪ ቡድን አባላት በሚመራው የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ ልዩነቱ እየተሰማን ነበር። የምናቀው ስሜት ነበረ።  ብዙ  አይነት ባህል ባለባቸው ቦታዎች ውስጥ በመጀመሪያ ስለ እርስ በእርሳችን ደህንነት እንጠያየቃለን ፣ የማኅበረሰብ እና የግለሰቦችን ፍላጎቶች እና ችግሮች በማጉላት እና መፍትሄዎችን ለማግኘት በክህሎት እንሰራለን። መሪ ኦሚቴው በተለመዱ አጀንዳዎች ላይ ለውጥ በማድረግና በየስብሰባዎቹ ላይ የሚነሱትን ርዕሶች የተሻለ የመወያያ ጊዜ ያላቸው እንዲሆኑ ጥቂት በማድረግና ችግሮቹ በጥልቀት እንዲመረመሩ አድርጓል። እነዚያ በአባላት የሚመሩት የመጀመሪያዎቹ ስብሰባዎች ፣ እና እነሱ የጠቆሙት የአስተሳሰብ ለውጥ ፣ ለእኛ የፈውስ ተሞክሮ ነበር።

ይህ አዲስ የአሰራር ለውጥ ( ቅርጽ)  የእኛን ከላይ የሚታዩ ልዩነቶችን ወደሚያጎሉ በርካታ መስቀለኛ መንገዶች አንቅቶናል። እንደነዚህ ያሉ ችግር ያላቸውን ቤተሰቦች  ፤ የአካል ጉዳተኛ ልጅ ፣ ወይም የምግብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ፣  ወይም የመጠለያ ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች ወደ PARCAG አጋሮቻችን እገዛ እንዲያገኙ በመላክ መፍትሄ ለመስጠት እየተሻሻልን ነው።

የተሰበረው እና ታሪክአዊ ዘረኛ የሆነው ሂደታችን በሰዎች እና በማህበረሰቦች ጤና ላይ በጥልቀትና  በብዙ መንገዶች  ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እናውቃለን። በ PARCAG ውስጥ ያገኘነው ተሞክሮ ምክንያት እነዚያን ተፅእኖዎች በደንብ እንድናይ እና ችግሮቹን ለሚገጥሟቸው ሰዎች የበለጠ የተሻሻለ የጤና እንክብካቤ እንድናቀርብ አድርጎናል።

ለዚህ ወረርሽኝ የድርጅታችን እና የእኛ የካውንቲ ማህበረሰብ ተኮር ምላሽ በየጊዜው እያደገ ነው - ከዝግመተ ለውጡ እረፍት የለም። እሱ ከባድ ተደጋጋሚ ሂደት ነው - በየቀኑ ስትነሳ ለመማር ዝግጁ መሆን አለብህ። እሱ ከባድ ስራ ነው ፣ እናም ስለራሳችን የያዝናቸውን ጽንሰ -ሀሳቦች ይፈትናል ፤ ነገር ግን ስርዓቶችን በትንሹና በከፍተኛ ሁኔታ ሊለውጥ ይችላል። በየግዜው ራሳችንን ለማሻሻልና ለመማር ቁርጠኛ

ነን ፤ እናም ይህንን ሥራ ከሚሠሩ እና እንደነዚህ ከባድ ውይይቶች ውስጥ ገብተው ውጤቱን አብረው ለማየት ከሚፈልጉ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በአንድ ጠረዴዛ ላይ በመገኘታችን በጣም ዕድለኞች ነን።

ይሄ ሥራ መሰናክሎች አሉት - ለሚታገሉ እና ለሚታገሉት ለማንኛውም ነገር ተገዢ በሆኑ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶች የጊዜ እና የክህሎት አቅም ይጠይቃሉ እናም ይህ ትልቅ ጥያቄ ነው። PARCAG ላይ የተወከሉት ትልልቅ ተቋማዊ ድርጅቶች ለመካፈል ፣ ለማዳመጥ ፣ ለመማር እና ለመሰተፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት በእጥፍ ማሳደግ አለባቸው።

ከዚህ ሥራ ነፃ የሆነ ተቋም የለም። በ ሬንየር ቫሊ አዋላጆች ( RVM) ውስጥ በ2021 ላይ ፍትሃዊ የሥራ ቦታን በመገንባት ራሳችንን ተጠያቂ ለማድረግ ከፍተኛ ለውጦችን አድርገናል። ይህም የሚጀምረው ከውስጥ-ወደውጭ የአመራር ልማት ፣ ለሠራተኞች እና ለቦርዱ ተከታታይ ሥልጠና በመስጠት ፣ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ እንድሆነ ተምረናል።

ይሄ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ፣ ጊዜ የሚወስድ ሥራ ስለሆነ እውቀትን የመካፈል ፣ እራስን ከፍ ሳያደርጉ የሌለውን ማህበረሰብ ትኩረት ማስጠት እንዲሁም አስተዋፃኦ ማድረግን ይጠይቃል ፤ ምክንያቱም ይሄን ማድረግ ትክክለኛው ተግባር ነው። PARCAG ሁላችንም እስከተሰተፍን ድረስ ሥራውን በጋራ መቋቋም የምንችልበት ጠረጴዛ ነው።

በእኛ ካውንቲ ውስጥ ላሉት ትልልቅ ገንዘብ ሰጪዎች ፣ እራሳቸውን የሚጠይቁበት ጊዜ ነው ፥ በማህበረሰቡ ውስጥ አቅም ለመገንባት ምን ዓይነት ሥራ መሥራት አለብን? ሰራተኞቻችን እና ማህበረሰቦቻችን ግቦቻቸውን እንዲያሳኩ ለመርዳት እንዴት መሥራት እንችላለን? የራሳችንን እሴቶች እና ዲዛይኖች በእውነተኛ ፍላጎቶቻቸው ላይ ለመጫን ከመሞከር ይልቅ በማህበረሰቡ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ጤና እያሳደግንና ሀብትን በውስጣቸው እንዲፈጥሩ እያደረግን ነው? ከማጥፋት ይልቅ እንዴት አስትዋጾ ማድረግና መፍጠርን እንችላለን?

PARCAG እርስ በእርሳችን ሰብዓዊነት እንዲኖረን ፈቅዶልናል - የዙም እረፍት ክፍሎች ትልቅ አመጣጣኞች ናቸው - ልክ እንደማህበረሰብ-ተኮር ድርጅቶች አለቆች የትልልቅ ተቋማት መሪዎች ከልጆቻቸው እና ከቤት እንስሳቶቻቸው እንዲሁም የበር ደወሎች እና በድካም ላይ ሆነው ይመጣሉ።

እነዚህ  ሁኔታዎች እርስ በእርስሳችን እንድንማር እና እንድንተዋወቅ በተጨማሪም አሁን በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ በጣም ወደሚያስፈልጉት ውስጣዊ እና ውጫዊ ለውጦች ለመጓዝ ይረዱናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።



*ከግራ ወደ ቀኝ- (1) የሬኒየር ቫሊ አዋላጅ ህፃን ልጅ(2) አርኔይድራ ኦስተን ፣ የሬንየር ቫሊ አዋላጆች ጤና አስተማሪ እና ለህብረተሰቡ ክፍት የሆነ በሳምንት ለሁለት ጊዜ የሚካሄድ የቅድመ ወሊድ ትምህርት ቡድኖች አዘጋጅ። እና(3) ጄን ሊ ንስታድ ፣ ፈቃድ ያላት አዋላጅ እና የሰሲ ደንከን (Ceci Duncan) መሪ ተማሪ አዋላጅ*

## ከባዱ ሥራ ገና በመጀመር ላይ ነው - 2021

የጥቁር ፣ የእስያ ፣ የፓስፊክ ደሴት እና የነባር ተወላጆችን ድምፆች እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶችን ማዕከል ማድረግ በእርግጥ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ኃይልንና ገንዘብን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማቆየት ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነት ሁኔታ ማለት ነው። በማህበረሰብ ሀሳቦች ላይ እርምጃ መውሰድና በማህበረሰቡ  ለሚመሩ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን እና ሀብቶችን ማቅረብ ማለት ነው።

እኛ ብዙውን ጊዜ በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ለማህበረሰብ ድርጅቶች የተዘጋቹትን ጥቅማ ጥቅም ያላቸውን ነጋሮች ተቀባዮች ነን ፣ ነገር ግን እነዚህ ጥቅሞች ብዙ ጊዜ እና ስራ የሚፈልጉ በመሆናቸው ጥቅሞቹን ከመተው ይልቅ መቀበሉ የበለጠ ዋጋ ያስከፍለናል።  ይህ በአነስተኛ ማኅበረሰብ-ያተኮሩ ድርጅቶች መካከል የተለመደ ተሞክሮ ነው ፣ ምንም እንኳን ለማህበረሰቡ አስፈላጊ የሆኑ ብዙ ሥራዎችን የምናደርግ ቢሆኑም ፣ በዚህ ምክንያት ነው ብዙ ግዜ ወደኋላ የምንቀረው።

የሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና በፖሊሲ አውጪነት ለማህበረሰቡ ወደ ትልቅ ሚና መሸጋገር ሲጀምር ፤ የፖለቲካና የጤና ሂደቶች ሊማሩ የሚችሉት እውነተኛ የሥልጣን መልሶ ማቋቋም

አቅም እድል አለ። ይህንን ሞዴል እጅግ ብዙ ከሆኑ ተወዳጅና በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ተቋማት ጋር እንዲሁም የሲያትልና ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና ሰራተኞችና አመራሮች ጋር በጋራ በመሆን ጊዜያችንን ተጠቅመን ጋራ ጥረቶችን በማድረጋችን ኮርተናል። ወደፊትም በ2021 የተጋራናቸውንና ቀጣይነት ያላቸውን ጥረቶች በጉጉት እንጠብቃለን።

*መጀመሪያ የታተመው መስከረም 1 ቀን 2021 ነው*